የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 36.
ADDIS ABABA 27th May, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፹/፪ሺ ዓ.ም

የኢትዮ-ስፔን አጠቃላይ የትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፩፻፫

CONTENTS

Proclamation No. 580/2008

Ethio-Spain General Agreement of Co-operation Ratification Proclamation Page 4103

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፹/፪ሺ

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በስፔን ኪንግደም መካከል የተደረገውን አጠቃላይ የትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በስፔን ኪንግደም መካከል እ.ኤ.አ ጃንዋሪ ፴ ቀን ፪ሺ፯ አጠቃላይ የትብብር ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፴ ቀን ፪ሺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮ-ስፔን አጠቃላይ የትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በስፔን ኪንግደም መካከል እ.ኤ.አ ጃንዋሪ ፴ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመው አጠቃላይ የትብብር ስምምነት ጸድቋል።

## PROCLAMATION NO. 580/2008.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE GENERAL AGREEMENT OF CO-OPERATION BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE KINGDOM OF SPAIN

**WHEREAS**, the General Agreement of Co-operation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of Spain was signed on the 30th day of January, 2007;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 8th day of May, 2008;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethio-Spain General Agreement of Co-operation Ratification Proclamation No. 580/2008".

**2. Ratification of the Agreement**

The General Agreement of Co-operation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kingdom of Spain signed in Addis Ababa on the 30th day of January, 2008 is hereby ratified;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፫. <u>ስምምነቱን በሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን</u>

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲያከናውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**3. Power of Implementation**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of this Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of May, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**